# ዳያስፖራ ኢንፎርሜ

# Diaspora Informer

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
ጀኔራል የሚዘጋጅ ታህሳስ 2005 ዓ.ም.

# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑፐሊክ መንግስት የሚሰጡ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች



# ዳያስፖራ ኢንፎርመር
# Diaspora Informer

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዳየስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀኔራል የሚዘጋጅ ታህሳስ 2005 ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐፐሊክ መንግስት
የሚሰጡ
የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች

# በመንግስት የሚሰጡ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች

## መንግስት ማበረታቻውን ለምን መስጠት አስፈለገው?

* የአገሪቱን ልማት ለማፋጠን በሚደረገው ጥረት የግሉን ሴክተር ሚና ለማሳደግ፣
* የአገሪቱን ሰፊ የተፈጥሮ ሃብት ጥቅም ላይ ለማዋልና ለማልማት፣
* ምርትን፣ ምርታማነትና አገልግሎት በማሳደግ የአገር ውስጥ ገበያ እንዲዳብር ማድረግ፣
* ወጪ ምርቶቸና አገልግሎቶች በመጠን፣ በዓይነት በጥራት እንዲጨምር በማበረታታት የውጭ ምንዛሪ ለማሳደግ፣
* ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት የውጭ ምንዛሪን ለማሳደግ፣
* በክልሎች መካከል የተመጣጠነ ዕድገትና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንዲፈጠር ማበረታታትና በኢኮኖሚ ዘርፎች መካከል ያለውን ትስስር ለማጠናከር፣
* የውጭ ኢንቨስትመንት በአገሪቱ ልማት ተገቢውን ሚና እንዲኖረው ለማድረግ፣
* ለኢትዮጵያውያን ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠርና ለአገሪቱ ዕድገት የሚያስፈልገውን የቴክኒክ ሙያ፣ የሥራ አመራር ዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማስፋፋት ነው፡፡

## በመንግስት የሚሰጡ የማበረታቻ ዓይነቶች

* ትርፍ ገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻ (Tax Holiday)
* ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ መሆን ማበረታቻ (Duty Free Privileges)

## የማበረታቻዎቹ ተጠቃሚዎች እነማን ናቸው?

* ማበረታቻ በሚሰጣቸው መስኮች የኢንቨስትመንት ፍቃድ በማውጣት (በግብርና ፣ ኢንዳስትሪ፣ ኮንስትራክሽን፣ የቱሪዝም አገልገሎት መስጫ ተቋማት፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት እና ሌሎች በደንብ ቁጥር 84/95 አንቀፅ 10 ክልከላ ያልተደረገባቸው ኢንቨስትመንቶች)፣
* በበጀት የሚተዳደሩ የኢትዮጵያ መንግስት መ/ቤቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት፣
* በማዕድን ምርመራ፣ ፍለጋና ምርት የተሰማሩ፣
* በነዳጅ ፍለጋ የተሰማሩ ባለሃብቶች፣

* ግብርና (የአበባ እርሻ ጨምሮ) ለተሰማሩ ባለሀብቶች ነው፡፡

## በኢንዱስትሪ

* ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች(ኢንዱስትሪ መንደር ግንባታ)

## በግብርና

* ግብርና (የአበባ እርሻ ጨምሮ)

## ማህበራዊ ዘርፍ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት

* ቱሪዝም መስጫ ተቋማት( ባለ ኮከብ ደረጃ ያለቸው ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ ሪዞርት ሆቴል፣ እስፔሻል ሬስቶራንት፣ ሎጅ እና የማስጎብኘት አገልግሎት)

* የትምህርት ተቋማት የጤና ተቋማት ሌሎች (ICT ፣ የማማከር አገልግሎት.....)

## የኮንስትራሽን ዘርፎች

* የሕንፃ ስራ ተቋራጭ (BC)፣

* ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ (GC)፣

* የመንገድ ስራ ተቋራጭ (RC)፣

* የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ማከራየት፣

* ልዩ ሥራ ተቋራጭንት፣

* የምሰሶ ጉድንድ ቁፋሮና ግንባታ ሥራ ተቋራጭንት፣

* የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ተቋራጭነት፣

* Real State (በReal State ላይ የተሰማራ ባለሀብት ከቀረጥና ታክስ ነፃ የካፒታል እቃን ማስገባት የማይችል ሲሆን ነገር ግን ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕቃዎች በውጭ አገር በዘላቂነት የሚኖሩ ኢትዮጲያውያን እና የውጭ ዜግነት ያላቸው የኢትዮጲያ ተወላጅ ባለሀብቶች ለኢንቨስትመንት ሥራቸው የሚሆን የካፒታል ዕቃ በፍራንኮ ቫሉታ ቀረጥና ታክስ ከፍለው እንዲያስገቡ ስለሚፈቅድ በዚሁ መሠረት የሚስተናገዱ ይሆናል፡፡)

## ማዕድን

* ማዕድን(ፍለጋና ማምረት)፣

* ነዳጅ ፍለጋ፣

# የሚሰጡ ማበረታቻዎች

## የገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻ

### የአምስት ዓመት የገቢ ግብር ነፃ

በማኑፋክቸሪንግ፣ በአግሮ ኢንዱስትሪ፣ የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ልማት እና የተመረጡ የግብርና ምርት ዓይ ነቶች /በመመሪያ የተወሰኑ/ በመሰማራት የሚሰጥ ሲሆን ባለሃብቱ 50% የሆነውን ምርቱን ውጤት ወይም የሚ ሰጠውን አገልግሎት ወደ ውጭ የሚልክ ከሆነ፣ ወይም 75% የሆነውን የምርቱን ውጤት ወይም የሚሰጠውን አገልግሎት ወደ ውጭ ለሚልክ ባለሃብት በምርት ወይም በአገልግሎት ግብአትነት ለሚያቀርብ ድርጅት ብቻ የመብቱ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

### የሁለት ዓመት የገቢ ግብር ነፃ

ባለሃብቱ ካመረተው ምርት ከ50% በታች የሚሆነውን ወደ ውጭ የሚልክ ወይም ምርቱን ለሃገር ውስጥ ገበያ ብቻ የሚያቀርብ ከሆነ ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብት ያገኛል፡፡

### በማስፋፊያ የሚሰጥ የገቢ ግብር ነፃ

በማኑፋክቸሪንግ፣ በአግሮ ኢንዱስትሪ፣ የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ልማት እና የተመረጡ የግብርና ምርት ዓይነቶች (በመመሪያ የተወሰኑ) ሥራዎች የተሰማራና ከሚያመርተው ምርት ወይም ከሚሰጠው አገልግሎት ቢያንስ 50% የሆነውን ወደ ውጭ የሚልክ ባለሃብት ምርቱን 25% በላይ በእሴት ካሳደገ ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብት ያሰጣቸዋል፡፡

### ልዩ ልዩ

* ከገቢ ግብር ነፃ የመሆኛ ዘመን መቆጠር የሚጀምረው ባለሃብቱ ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ይሆናል፡፡
* ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብት በተሰጠበት ዘመን ውስጥ ኪሳራ ያጋጠመው ማንኛውም ባለሃብት የገቢ ግብር ነፃ መብቱ ዘመን እንዳለቀ ለግማሽ የነፃ መብቱ ዘመን የደረሰበትን ኪሳራ ማስተላለፍ ይችላል፡፡

# የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ

### ካፒታል ዕቃዎች

* ማንኛውም በኢንዱስትሪ፤ በአግሮ ኢንዱስትሪ፤ በግብርና እና ማህበራዊ ዘርፍ በኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚሰማራ ባለሃብት ለሚያቋቁመው አዲስ ድርጅት፣ ወይም ነባር ድርጅቱን ለማስፋፋት ወይም ለማሻ ሻል የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎች
* የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብት ያለው ባለሃብት ለነባር ድርጅቱ የሚያስፈልገውን የካፒታል ዕቃ፣ የማዕድን ምርመራ ባለፍቀዱ ወይም የእርሱ ተቋራጭ ባፀደቀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት፣ ማሽነሪዎችን ፣ መሣ ሪያዎችንና፣
* የማዕድን ማምረት (አነስተኛና ከፍተኛ) ባለፍቃዱ ወይም የእሱ ተቋራጭ በፀደቀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት መሣሪያዎችን እና ማሽነሪዎችን ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሊያስገባ ይችላል፡፡

## የግንባታ ዕቃዎች

* ማንኛውም በኢንዱስትሪ፣ በአግሮ ኢንዱስትሪ፣ በግብርና እና ማህበራዊ ዘርፍ የሚሰማራ ባለሃብት ለሚ ያቋቋመው አዲስ ድርጅት፣ ወይም ነባር ድርጅቱን ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል የሚያስፈልጉ የግንባታ ዕቃዎች ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሊያስገባ ይችላል፡፡

## መለዋወጫዎች

በኢንቨስትመንት ለገቡ የካፒታል ዕቃዎች ከዋጋቸው 15% የማይበልጥ መለዋወጫዎች በ5 ዓመት የጊዜ ገደብ

የማዕድን ምርመራ ባለፍቀዱ ወይም የእርሱ ተቋራጭ ባፀደቀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት አላቂ ዕቃዎችን

የማዕድን ማምረት (አነስተኛና ከፍተኛ) ባለፍቃዱ ወይም የእሱ ተቋራጭ በፀደቀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት አለቂ ዕቃ ስራ ለማስጀመር ለ3 ወር ማስገባት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቅድለታል፡፡

## ተሽከርካሪዎች

ለማምረታቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች የጭነት መኪና፣ ዴሊቨሪ ቫን፣ ፍሪጅ የተ ገጠመለት የጭነት መኪና፣ ጀልባና ፒክ አፕ ሲሆኑ ባለሃብቱ ቢያንስ 10 ሚሊዮን ብር ኢንቨስት ማድረግ ይጠበ ቅበታል፡፡የልማት አካባቢ መሰረት አድርጎ ይሰጣል፡፡

10 ሚሊዮን ብር ኢንቨስትመንት የሚያጠቃልለው

የህንጻ ወጪዎች------------------------------------------- xxxx

ለካፒታል ዕቃዎች ግዥ------------------------------------ xxxx

የመሬት ሊዝ ክፍያ----------------------------------------- xxxx

ምርት ማምረት ከመጀመሩ በፊት ያሉ ወጪዎች---------- xxxx

ሥራ ማስኬጃ------------------------------------------------ xxxx

ጠቅላላ-------------------------------------------> = 10 ሚሊዮን ብር

- በግብርና ኢንቨስትምንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች ፒክ አፕ፣ ሞተር ብስክሌት፣ ማቀዝቀዣ የተገጠመ ለት የጭነት መኪናና ቶም ካር ሲሆኑ በሚያለሙት የመሬት ስፋት፣ በሚኖራቸው የእንስሳት ብዛት መሰረት በማድረግ ይሰጣሉ፡፡ የልማት አካባቢ መሰረት በማድረግ ይሰጣሉ፡፡
- ለባለ ኮከብ ደረጃ ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ ሬስቶራንትና የሎጅ አግልግሎት ኢንቨስትመንት በኮከብ ደረጃ ቸው መሰረት ፒክ አፕ ይፈቀድላቸዋል፡፡
- ለማስጎብኘት አገልግሎት የሚውሉ አውቶብስ እና ስቴሽን ዋገኖች ይፈቅዳሉ፡፡
- ማንኛውም ባለሃብት ለሰራተኞች የአደጋ ጊዜ አገልግሎት የሚውሉ አምቡላንሶችን ከቀረጥ ነፃ ያስገባል፡፡

- በኢንዱስትሪ ዞን ግንባታ የሚሰማራ ማንኛውም ባለሃብት 3 ፒክ አፕ ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማስገባት ይቻላል፡፡

## ለኮንስትራክሽን ፣ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ፣ ለምሰሶ ጉድጓድ ቁፋሮ እና ግንባታ ፣ ለልዩ ሥራ ተቋራጭነት የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

የከተማ ልማትና ኮንሰትራክሽን ሚኒስቴር ለደረጃው እንደሚያስፈልጉ ከዘረዘራቸው መሳሪያዎች በዋጋ ሃያ አምስት በመቶ (25%) ያህሉን ማሳየት አለባቸው፣

ለውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ እና ለመሰረት ጉድጓድ ቁፋሮና ግንባታ ስራ ተቋራጭነት የኢንቨስትመንት የስራ መስኮች ድርሊንግ ሪጉ ወይም ጉድጓድ መቆፈሪያው መሳርያ ከተገዛ በኃላ ይፈቀድላቸዋል፡፡

የሚፈቀዱት የተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት የሚወሰነው በዘርፍ፣ በደረጃቸውና በሚያስገቡት ድርሊንግ ሪጉ ወይም ጉድጓድ መቆፈሪያው መሳርያ መሰረት በማድረግ ነው፡፡

## ለመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ (ICT) ልማት ኢንቨስትመንት መስክ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

| የቋሚ ሰራተኞች ብዛት | የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት |
|---|---|
| 50 | 1 አውቶብስ ወይም 2 ሚኒባስ እና 1 ዴሊቨሪ ቫን |
| ከ50 በላይ - 100 | 2 አውቶብስ ወይም 3 ሚኒባስ እና 1 ዴልቨሪቫን |
| ከ100 በላይ | 3 አውቶብስ ወይም 4 ሚኒባስ እና 2 ዴልቨሪቫን |

## በማዕድን ዘርፍ ስለሚገቡ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

የሚፈቀድላቸው የተሽከርካሪዎች ብዛትና ዓይነት የሚወሰነው በምርትና በፍለጋ በመከፈል፣እንዲሁም ኢንቨ ስት በሚያደርጉት የካፒታል መጠን ነው፡፡

## ለሰራተኞች ሰርቪስ የሚፈቀዱት የተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት

| የሰራተኞች ብዛት | የሥራ መስክ | የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት |
|---|---|---|
| ከ25-50 | ኢንቨስትመንት | 2 ሚኒባስ ወይም 1 አውቶቢስ |
| ከ50 በላይ | ኢንቨስትመንት | 3 ሚኒባስ ወይም 2 አውቶቢስ |
| ከ10-12 | ማዕድን | 1 አነስተኛ አውቶብስ |
| ከ13-50 | ማዕድን | 2 አነስተኛ ወይም 1 መካከለኛ አውቶብስ |
| ከ50 በላይ - 500 | ማዕድን | ለእያንዳንዱ ተጨማሪ 50 ሰራተኛ 1 አነስተኛ ወይም መካ ከለኛ አውቶብስ |

## የተሸከርካሪ ማበረታቻ የማይፈቀድላቸው የማምረቻ ኢንዱስትሪ ሥራ መስኮች

- ዱቄት፣ ዳቦ፣ ኬክ እና/ ወይም አይስ ክሬም ማምረቻ፣
- ተበጥብጦ የሚታሸግ ጁስ ማምረት፣
- የትንባሆ ውጤቶችን ማምረት፣
- ጣውላ እና /ውይም ሞራሌ ማምረት፣
- የቤት ክዳን ቆርቆሮ ወይም ምስማር ማምረት፣
- የአስቤስቶስ ውጤቶችን ማምረት፣
- ጠጠር ወይም ብሎኬት ማምረት፣
- የሚዲያ ውጤቶችን ማምረት ወይም ማባዛት፣

## የቀረጥ ነፃ መብት ስለማስተላለፍ

ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆኖ የገባ ማናቸውም የካፒታል ዕቃ ሊከፈልበት ይገባ የነበረው የጉምሩክ ቀረጥ አስቀድሞ ሳይከፈልበት ተመሳሳይ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብት ለሌላ ሰው ሊተላለፍ አይችልም፡፡

## ኢንቨስትመንት ማበረታቻ የማይፈቀድላቸው የስራ መስኮች

ሀ/ ባለ ኮከብ ደረጃዎችን የማይጨምሩ ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ ፔንሲዮኖች፣ ሻይቤቶች፣ ቡናቤቶች፣ መጠጥ ቤቶች፣ የምሽት ክበቦች፣ ዓለም አቀፍ ደረጃ የሌለው ሬስቶራንቶች፣ ምግብ ቤቶች፣

ለ/ የንግድ ሥራዎች ማለትም የጅምላ የችርቻሮና አስመጪነት ሥራ

ሐ/ የጥገና አገልግሎት ሥራ፣

መ/ የንግድ መንገድ ትራንስፖርት፣ የመኪና ማከራየት አገልግሎት ሥራ፣

ሠ/ የፖስታና ኩሪየር አገልግሎት ሥራ፣

ረ/ ለንግድ መኖሪያ ቤት የሚሆን ቤቶችና ሕንፃዎችን ሠርቶ ማከራየትና መሸጥ፣

ሰ/ የንግድ አስተዳደር አማካሪነት ሥራ፣

ሸ/ የማስታወቂያ ሥራ አገልግሎት፣

ቀ/ የፊልምና መሰል ሥራዎች፣

በ/ የሬዲዮና ቴሌቪዥን ስርጭት አገልግሎትሥራ፣

ተ/ የሲኒማና የቲያትር ቤቶች አገልግሎት ንግድ ሥራ፣

ቸ/ የጉምሩክ አስተላላፊነት ንግድ ሥራ፣

ኀ/ የላውንደሪ አገልግሎት ንግድ ሥራ፣

ነ/ የጉዞ ወኪልነት የንግድ ረዳትነት የትኬት መሸጫ አገልግሎት ንግድ ሥራ፣

ኘ/ የሎተሪና የመሳሰሉት ሥራዎች፣

## የተሰጡ መብቶች ለማግኘት ማሟላት የሚገባቸው ዋና ዋና ሰነዶች

### 1. <u>የካፒታል ዕቃዎችን ለማስገባት መሟላት ያለባቸው ሰነዶች</u>

- የኢንቨስትመንት ፈቃድ የታደሰ
- ኮሜርሻል ኢንቮይስ /COMMERCIAL INVOICE/
- ማስጫኛ ሠነድ /BILL OF LOADING, AIR WAY BILL OR TRUCK WAY BILL/
- ፓኪንግ ሊስት /PACKING LIST/
- የባንክ ፈቃድ /BANK PERMIT/
- ማመልከቻ
- ቲን /Tax Identity Number/
- የንግድ ሥራ ፈቃድ /BUSSINESS LICENCE/ / ሥራ የጀመረ ከሆነ የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ

### 2. <u>የግንባታ ዕቃዎችን ለማስገባት መሟላት ያለባቸው ሰነዶች</u>

የካፒታል ዕቃ ለማስገባት ከሚጠየቁ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ

- የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ /ፕሮጀክቱ ተጠቅሶ/
- የግንባታ ፈቃድ /ፕሮጀክቱ ተጠቅሶ/
- BILL OF QUANTITY /ፕሮጀክቱ ተጠቅሶ/
- BILL OF QUANTITY ያዘጋጀው የባለሙያ የንግድ ሥራ ፈቃድ የታደሰ
- የግንቦታ ዕቃዎች የተቀናነሰበት ፎርም ላይ ተሞልቶ ሊቀርብ ይገባዋል፡፡

### 3. <u>መለዋወጫዎችን ለማስገባት መሟላት ያለባቸው ሰነዶች</u>

በካፒታል ዕቃ ለማስገባት ከሚጠየቁት ከተዘረዘሩት ተጨማሪ

መለዋወጫ የተጠየቀበት መሣሪያ የቀረጥ ነፃ ደብዳቤ ከኢንቮይሱ እና አገር ውስጥ የገባበት ዲክላራሲዮን እንዲሁም ስሌቱ ተሰርቶ ሊቀርብ ይገባል፡፡

## 4. ተሽከርካሪዎችን ለማስገባት መሟላት ያለባቸው ሰነዶች
(ፒክ አፕ፣ ሞተር ብስክሌት፣ ማቀዝቀዣ የተገጠመለት የጭነት መኪናና ቶም ካር)

በካፒታል ዕቃ ለማስገባት ከሚጠየቁት ከተዘረዘሩት ተጨማሪ፡-

- የመሬት ይዞታ /ህጋዊ የኪራይ ውል/፣
- የድጋፍ ደብዳቤ ፕሮጀክቱ ከሚገኝበት ክልል ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት፣
- ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ ካፒታል ዕቃዎች እና የተገዙበት መረጃ፣
- መረጃ ከአገር ውስጥ ከሆነ ከቫት ተመዝጋቢ የተገዙ መሆኑን እና ዋጋቸዉ ተደምሮ ከ 10 ሚሊዮን ብር በላይ ሊሆን ይገባል፡፡ ከውጭ አገር የገዙ ከሆነ ቀረጥ ነፃ የገቡበት ደብዳቤ ከነኢንቮይሱ እንዲሁም ዲክላራሲዮን እና ማስጫኛ ሠነድ ሊያቀርቡ ይገባል፡፡

## 5. የሠራተኛ ሰርቪስን ለማስገባት መሟላት ያለባቸው ሰነዶች

በካፒታል ዕቃ ለማስገባት ከሚጠየቁት ከተዘረዘሩት ተጨማሪ

- የመሬት ይዞታ /ህጋዊ የኪራይ ውል/፣
- የድጋፍ ደብዳቤ ፕሮጀክቱ ከሚገኝበት ክልል ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት፣
- ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ ካፒታል ዕቃዎች እና የተገዙበት መረጃ፣
- የተገዙበት እና ከውጭ አገር የገዙ ከሆነ ቀረጥ ነፃ የገቡበት ደብዳቤ ከነኢንቮይሱእንዲሁም ዲክላ ራሲዎን እና ማስጫኛ ሠነድ ሊያቀርቡ ይገባል፡፡
- PAY ROLL ከገቢ ግብር ደረሰኝ ጋር የሦስት ወር የቋሚ ሠራተኛ ዝርዝር በተጨማሪ ሊቀርብ ይገባል፣

## 6. ከባንድድ ዌር ሃውስ ለሚገዙ መሳሪያ/ዎች እና ተሽከርካሪ/ዎች መሟላት ያለባቸው ሰነዶች

- የቀጠሮ ፎርም
- ማረጋገጫ ፎርም
- ለገዥ - ኢንቨስትመንት ፍቃድ የታደሰ
- የታደሰ ንግድ ፍቃድ (ስራ ከጀመሩ)

- ከባንድድ ዌር ሃውስ የተፃፈ ኦርጅናል ደብዳቤ
- የታደሰ የመጋዘን ፍቃድ
- የሽያጭ ውል
- Commercial Invoice, Bank permit ,Bill of Loading & declaration (each 1 copy)

## 7. ዝውውርን ለመፈፀም ለማስገባት መሟላት ያለባቸው ሰነዶች

| ሻጭ | ገዥ |
|---|---|
| ንግድ ፍቃድ (የታደሰ) | ማመልከቻ |
| የታደሰ ኢንቨስትመንት ፈቃድ | የታደሰ ኢንቨስትመንት ፈቃድ |
| ክሊራንስ | ቲን ሰርቲፊኬት |
| የሽያጭ ውል | |
| ዕቃው ከቀረጥ ነፃ የገባበት ደብዳቤ፣ | |
| ማመልከቻ | |
| ኢንቮይስ፣ | |
| ዲክለሬሽን | |
| ተሽከርከሪ ከሆነ ሊብሬ ኮፒ | |
| የሽያጭ ውል | |

## የገቢ ግብር እፎይታ ነፃ ስለመሆን

- ማመልከቻ ፣ ኢንቨስትመንት ፍቃድ ፣ የታደሰ ንግድ ፍቃድ
- መሬት ይዞታ /ህጋዊ ኪራይ ውል
- 25% እሴት ማሳደጉ ድጋፍ ደብዳቤ(በExpansion Investment ለሁለተኛ ጊዜ ሲጠይቁ)
- VAT Certificate (8 copy)
- TIN Certificate (8 copy)
- ለሀገር ውስጥ አቅራቢ የሽያጭ ደረሰኝ ኮፒዎች ወይም

- ለውጭ አቅራቢ ከሆኑ የድጋፍ ደብዳቤ ከኢንቨስትመንት ፅ/ቤት ምርት ማምረት የጀመረበት ቀን ፣ የት እንደሚሸጡ ፣ ውጪ አገር የሚልኩ ከሆነ ምን ያህል ፐርሰንት እንደሆነ

## በምትክነት ዕቃ/ዎች ለማስገባት

- ወደ ሀገር የገባው እቃ ጋር በአባሪነት የቀረቡ የቀረጥ ነፃ ደብዳቤ ከነ ኢንቮይስ ፣ የባንክ ፍቃድ እና ክሊራንስ፣
- ላኪው ዕቃው እንዲላክለት የገለፀበትን ደብዳቤ ከዋናው ጋር የተመሳከረ ኮፒ፣
- አስመጪው በዋረንቲ ሰርተፍኬት ላይ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ከአገር እንዲወጡ እና በምትክ ነት ተመሳሳይ ዕቃ እንዲላክላቸው ጥያቄ ያቀረበበትን ኮፒ፣
- ላኪው ሰለ ዕቃው የሰጠው ዋረንቲ ሰርተፍኬት ከዋና ጋር የተመሳከረ ኮፒ፡፡

## ማበረታቻዎቹን ለመስጠት የሚያስችሉ የህግ መሰረቶች

### አዋጆች

- አዋጅ ቁጥር 769/2004የኢንቨስትመንት አዋጅ
- አዋጅ ቁጥር 280/1994 እና ማሻሻያው 375/1995 የኢንቨስትመንት አዋጅ
- አዋጅ ቁጥር 678/2002 የማዕድን አዋጅ
- አዋጅ ቁጥር 295/1978 የነዳጅ ፍለጋ አዋጅ
- አዋጅ ቁጥር 622/2001 የጉምሩክ አዋጅ

### ደንቦች

- ደንብ ቁጥር 84/1995 እና ማሻሻያው 146/2000
- ስለ ኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ
- ደንብ ቁጥር 88/1995
- ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕቃዎች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

## መመሪያዎች

- (መመሪያ ቁጥር 1/2001) በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ልማት የኢንቨስትመንት መስክ ከገቢ ግብርና ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የመሆን ማበረታቻ የሚሰጥባቸው የሥራ መስኮችና ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የሚገቡ የቴክኖሎጂ መሣሪያዎችን ዓይነት ለመወሰን የወጣ መመሪያ
- (መመሪያ ቁጥር 4/2001) በማዕድን ዘርፍ ስለሚገቡ ተሽከርካሪዎች የወጣ መመርረያ
- (መመሪያ ቁጥር 3/2003) እና ማሻሻያ 4/2003 በኢንቨስትመንት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የሚገቡበት መመሪያ
- (መመሪያ ቁጥር 5/2003) የአስጎብኝነት የሥራ መስክ የሚውሉ አውቶቢሶችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ
- የአምስት ዓመት የገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻ የሚያገኙ የግብርና ምርት ዓይነቶችን ለመወሰን በኢንት ዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ የወጣ መመሪያ
- መመሪያ ቁጥር 52/2003
- ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ አገር ውስጥ ገብተው ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው ተሽከርካሪዎችን የቀረ ጥና ታክስ አከፋፈል ሁኔታን ለመወሰን የወጣ መመሪያ
- መመሪያ ቁጥር 66/2004
- ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕቃዎች ለመወሰን የወጣ መመሪያ

## ሰርኩላሮች እና ቃለጉባኤዎች

- በባለሥልጣን መ/ቤቱ፣ በኢንቨስትመንት ቦርድ፣ በማዕድን ሚኒስቴር እና በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚተላለፍ ሰርኩላሮች እንዲሁም የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲና ገቢዎች ሚኒስቴር በጋራ ባስተላለፋት ቃለ ጉባኤ መሠረት ማበረታቻዎችን ይሰጣል፡፡




"... የውጭ ኢንቨስተር 190 ምናምን አማራጭ አገር አለው
እናንተ ግን አማራጭ የላችሁም አንድ አገር ብቻ ነው ያላችሁ።"

የቀድሞ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠ/ሚኒስትር ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ
ለኢትዮጵያ ዳያስፖራ በስብሰባ ከተናገሩት የተወሰደ።

Designed & Printed by: http://www.masterprintingpressplc.com